ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ (አኢጋን)

# “የሴቶችን መብት በማስከበር ለሥልጣን ማጎናጸፍ”

## በሚል ለተዘጋጀው የኢትዮጵያውያን ሴቶች ዓለምዓቀፍ ጉባዔ
## የአቶ ኦባንግ ሜቶ መልዕክት

የተከበራችሁ የአገሬ ሴቶች፤

ይህንን ታላቅና ዓለምዓቀፍ ጉባዔ በማዘጋጀት እየተሳተፋችሁ የምትገኙትን በሙሉ እጅግ የከበረ ሰላምታዬን በአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ እንዲሁም በራሴ ስም ሳቀርብላችሁ ከፍተኛ ደስታ እየተሰማኝ ነው፡፡

ይህንን ጉባዔ የተሳካ እንዲሆን ላዘጋጃችሁትና ለተሳተፋችሁት በሙሉ በተለኝም **ለኢትዮጵያውያን ሴቶች ጉባዔ አስተባባሪ ኮሚቴ (ኢሴጉአኮ - EWCCC)** ያለኝን ታላቅ አክብሮት እንድገልጽ ይፈቀድልኝ፡፡

እንደምታውቁት ከእናንተ መካከል ተገኝቼ ይህንን ጉባዔ ለመሳተፍ ከፍተኛ ፍላጎት ቢኖረኝም ባጋጠመኝ የሥራ መደራረብ ለመገኘት አልቻልኩም፡፡ ነገር ግን ከእናንተ ጋር በመንፈስ መሆኔን እንድታውቁልኝ እፈልጋለሁ፡፡ በመሆኑም በአዲሲቷ ኢትዮጵያ ግንባታ ሴቶች ከፍተኛ አስተዋጽዖ እንደሚኖራቸው አሁን እናንተ የምታደርጉት ማስረጃ በመሆኑ ለእኔ ብቻ ሳይሆን ለመላው ሰላምና ፍትሕ ወዳድ ሕዝባችን ትልቅ ተስፋን የሚሰጥ ነው፡፡

በአሁኑ ጊዜ አገራችን መጠነ ሰፊና ዘርፈ ብዙ ችግሮች ውስጥ ትገኛለች፡- የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚ፣ የማኅበራዊ፣ የመንፈሳዊ፣ የጸታ፣ ወዘተ ከሚጠቀሱት ጥቂቶቹ ናቸው፡፡ በሁሉም ዓይነት ዓለምዓቀፋዊ መስፈርቶች አገራችን በመጨረሻው መስመር ላይ እንደምትገኝ በየጊዜው የምናነበው መረጃ ማስረጃችን ነው፡፡ በመሆኑም የአገራችን ሕዝብ በእንደዚህ ዓይነት አስቸጋሪ የሕይወት አዙሪት ውስጥ በሚገባበት ወቅት ከማንኛውም የኅብረተሰብ ክፍል ይልቅ የበለጠውን መከራና ግፍ የሚሸከሙት ሴቶች እንደሆኑ እሙን ነው፡፡ **በዚህ ሁሉ ውስጥ ግን የአገራችን እናቶች ልጆቻቸውን በመንከባከብ፣ በማሳደግና ከጥቃት በመከላከል ኅብረተሰባችን**

የጀርባ አጥንት በመሆን ቢያገለግሉም የሚገባቸውን ምስጋና ተነፍገዋል፤ ከፈጣሪ የተሰጣቸው መብትም ተረግጧል፡፡

ስለ ሴቶች መብት ስንናገር በዋነኛነት የምንጠቅሰው መሠረታዊ ስለሆነው የሰው ልጆች መብት ሲሆን ይህም ስለ ሴት አያቶቻችን፣ እናቶቻችን፣ እህቶቻችንና ሴት ልጆቻችን መብት መሆኑ አይዘነጋም፡፡ በመሆኑም መሠረታዊ በሆነው የሴቶች መብትና በሌሎች ሰዎች መብት መካከል የምንፈጥረው ምንም ዓይነት ድንበርም ሆነ መለያ ክልል ሊኖር አይችልም፡፡ ይልቁንም የሴቶች መብት እንደሚገባው ባለመከበሩ የበለጠ ተሟጋችና ለመብታቸው የሚቆሙ ተከራካሪዎች ሊኖሯቸው እንደሚገባ የሚስተዋል ነው፡፡

ከዚህ አኳያ የግል ታሪኬን ብጠቅስላችሁ፤ አሁን ለምገኝበት የማኅበራዊ ፍትሕ መስፈንና የሰብዓዊ መብት ተሟጋችነት ሥራ እንበቃ ያደረገችኝ ሴት አያቴ በመሆኗ ውለታው ሁሉ የእርሷ ነው በማለት በድፍረት እናገራለሁ፡፡ ልጅ ሳለሁ ሴት አያቴ የለገሰችኝ ርኅራሄ እንዲሁም ፍትሕንና ሐቅን በተመለከተ የነበራት ጠንካራ አቋም አሁን ለምሰራው ሥራ መሠረት የጣለ ነው፡፡ እናቴ መንታ ከወለደች በኋላ በርካታ ጊዜዬን አሳልፍ የነበረው ከሴት አያቴ ጋር ነበር፡፡ አያቴ ለሰዎች ታሳይ የነበረው ቅንነትና ለሚፈጸሙ በደሎች ደግሞ ያለ አንዳች ፍርሃት በድፍረት በመናገር ታሳይ የነበረው ቆራጥነት እኔ አሁን ያለሁበትን ማንነቴን የወሰነ ተግባር ነው፡፡ መንፈሳዊ ዓይኖቿ ተከፍተው እንዲህ ዓይነት የሰውን ማንነት የሚያስከብሩ ተግባራትን ያከናወነች ቢሆንም ማየት የተሳናት በመሆኗ የሌሎች ዕርዳታ ያስፈልጋት ስለነበር እስካሁን ድረስ በኢትዮጵያ “የሴቶች ሥራ ነው” እየተባለ የሚጠቀሰውን እንጨት መሰብሰብና የመሳሰለውን ሥራ በመሥራት አግዛት ነበር፡፡ በዚህ ሁሉ ውስጥ እናቴም ሆነች ሴት አያቴ በእንዴት ዓይነት አስከፊ የኑሮ መከራ ውስጥ ያልፉ እንደነበር በየጊዜው የምታዘበው የህይወት ገጠመኝ ነበር፡፡ ይህም ሁኔታ አሁን ላለሁበት የመብት ተሟጋችነት ያበቃኝ በመሆኑ ሁልጊዜ ሳወሳው እኖራለሁ፡፡

በአሁኑ ጊዜ ከአገራችን ሕዝብ ቁጥር ግማሽ ያህሉ ሴቶች ቢሆኑም በፖለቲካው መስክ ያላቸው ተሳታፊነትም ሆነ ውክልና እጅግ አናሳ ነው፡፡ በአገራችን ላይ ተንሰራፍቶ የሚገኘውን አገዛዝ እንደ አፓርታይድ በዘር፣ በፖለቲካ አመለካከት፣ ወዘተ ከፋፋይ ነው እያልን የምንናገር ቢሆንም በጾታ ረድፍም የሚከፋፍል መሆኑን የምንዘነጋው አይመስለኝም፡፡ በዚህም ከፋፋይ ስርዓት የበለጠውን የግፍ ሸክም የተሸከሙት ሴቶች መሆናቸው በግልጽ የሚታይ እውነታ ነው፡፡ በቤት ከሚደርስባቸው ጥቃት ጀምሮ በሥራ ቦታም ሆነ በተለያዩ ቦታዎች የሚደርስባቸው አስከፊና አሳፋሪ መድልዖ፣ ግፍ፣ ሰቆቃ መቆም አለበት! በአዲሲቷ ኢትዮጵያ እንዲህ ዓይነቱ ተግባርና የጾታ መድልዖ ፈጽሞ ቦታ አይኖረውም!!

ክቡራት የአገሬ ሴቶች፤

እናንተ አሁን ከምትገኙበት የምዕራቡ ዓለም ጋር ፈጽሞ ሊወዳደር በማይችል መልኩ በከፍተኛ መከራ ውስጥ የሚገኙት የአገራችን ሴቶች በተለይ በትምህርት ዘርፍ የሚታየው ልዩነት ሳይጠቀስ የሚታለፍ አይደለም፡፡ እኔ ከመጣሁበት የጋምቤላ ክልልም ሆነ እንደ አፋር፣ ቤንሻንጉል ጉሙዝና ሌሎች የተረሱና የተተዉ ቦታዎች በትምህርት ገበታ ላይ የሚገኘው የሴቶች ቁጥር እጅግ ዝቅተኛ ሲሆን በሌሎች ጠቅላይ ግዛቶችም ከዚህ የተለየ እንደማይሆን ለመገመት አያዳግትም፡፡

**ታዲያ ይህ ሁሉ እየሆነ ሴቶችን ያላሳተፈና ያላሳፈረ የነጻነት፣ የፍትሕ፣ የሰላምና የብጽግና ባቡር ከታሰበበት የነጻነት ጣቢያ መድረስ ይችላል ወይ? መልሱ "ፈጽሞ በጭራሽ አይሆንም" የሚል ነው፡፡ ጥቂቶች በግላቸው ተሳክቶላቸው የተቀረው አብሮ ያልፍለታል የሚባል አስተሳሰብ ፈጽሞ የማይሠራ ነው፡፡ በመሆኑም የአገራችንን ግማሽ ሕዝብ ያላካተተ የአዲሲቷ ኢትዮጵያ ምሥረታ ስኬቱ ያማረ እንደማይሆን የሚያጠራጥር አይደለም፡፡ ቢመሰረትም እንኳን ራሱን ለጥፋት ያዘጋጀ እንደሚሆን እሙን ነው፡፡**

ዛሬ በርካታ ወጣት ወንዶች ቤተሰባቸውን፣ የትዳር ጓደኛቸውንና አገራቸውን ጥለው ሲሰደዱ ካሰቡበት ሳይደርሱ እንደወጡ የሚቀሩት ቁጥር ቀላል አይደለም፡፡ ይህ በሚሆንበት ጊዜ አገር ቤት የሚቀሩት ሴቶች ናቸው የበለጠውን የኑሮ ሸክም የሚሸከሙት፡፡ **እንደ እስክንድር ነጋ ዓይነቶች ስለ ፍትሕ ሲናገሩና እስርቤት ሲወረወሩ የቤተሰባቸው ኃላፊነት የሚወድቀው በትዳር ጓደኞቻቸው ጫንቃ ላይ ነው፡፡ እንደ እህት፣ ጓደኛና መሪ ከማከብራቸው ሴቶች መካከል አንዷ የሆነችው ብርቱካን ሚደቅሳ እስርቤት ስትገባ ህጻን ልጇን የማሳደግና መላውን ቤተሰብ የመንከባከብ ኃላፊነት የእናቷ እንደነበር ሁላችንም የምናውቀው ነው፡፡**

የኢትዮጵያ ሴቶች ሁኔታ በዚህ የሚያልቅ ብቻ አይደለም፡፡ **በአረብ አገራት ሥራ ለማግኘት በሚያደርጉት የኑሮ ትግል የሚደርስባቸው ግፍና መከራ ለመገንዘብ የእህታችን ሸዋዬ ሞላን ታሪክ መቃኘቱ ብዙ የሚናገረው አለ፡፡** እንደ ሸዋዬ ያሉ እጅግ በርካታ ሴቶች የሚደርስባቸውን መከራና ሰቆቃ ለድርጅታችንም ሆነ ለእኔ በግል በየጊዜው የሚነግሩኝ በመሆኑ የእያንዳንዳቸውን የህይወት ገጠመኝ አሁን ልዘረዝር የምችለው አይደለም፡፡ **በሊባኖስ ቤይሩት ከተማ በአደባባይ ስትደበደብ እና መሬት ለመሬት ስትጎተት የተመለከትናት ሌላዋ እህታችን ትዕይንት እንደ ሕዝብ የውርደታችንን ዝቅጠት የሚያመለክት ብቻ ሳይሆን ማብቂያ የሌለውን የእህቶቻችንን ሰቆቃ በግልጽ የሚያሳይ ዕለታዊ ክስተት ነው፡፡ በተለይ ደግሞ**

**ድርጊቱ በኢትዮጵያ ቆንስላ ጽ/ቤት ፊት ለፊት መከሰቱ መንግሥት አልባ ለመሆናችን ሌላው ማረጋገጫ ነው፡፡ እነዚህ ውብ እህቶቻችን እስከመቼ እንደዚህ ከሰውነት ተራ ወጥተው ይኖራሉ? እስከመቼስ ጠባቂ እንደሌለው አገር አልባ ሆነን እንኖራለን?**

ውድ እህቶቼ፣

ሁላችንም የዜጎች መብት የሚከበርባትን አዲሲቷን ኢትዮጵያ ለመመሥረት እናልማለን፤ ተስፋም እናደርጋለን፡፡ **ሆኖም ግን የአዲሲቷ ኢትዮጵያ ምስረታ እውን የሚሆነው እንደዚህ የተሰበሰባችሁትን ሴቶችንና ሌሎችንም ጨምሮ ሁሉንም ለሥልጣንና ለመብት መከበር በሚያበቃ መልኩ ሲከናወን ብቻ ነው፡፡ አሁን ከገባንበት የማያቋርጥ የዘርና የጎሣ አዙሪት መውጣት እንችል ዘንድ በፍቅርና በእኩል ዓይን እያየች የምትመግበንና የምታሳድገን እናት ታስፈልገናለች፡፡ ወደዚህ ምድር የምታመጣውን ህይወት ተንከባክባ የምታሳድግ ዓይነት እናት ከመካከላችን ለማስነሳት ፈጣሪ እናንተ ሴቶችን እየተመለከታችሁ ነው፡፡ በአገራችን ደም መፋሰስ፣ የዘር ጥላቻና መከፋፈል እንዲያበቃ መንገዱን ሊያሳዩን የሚችሉት ሴቶች ናቸውና ይህንን ጉዳይ አጥብቃችሁ እንድታስቡበት ላስገነዝባችሁ እወዳለሁ፡፡**

በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የተጠቀሰችው የአስቴር ታሪክ ለዚህ ገጣሚ ምሳሌ ነው፡፡ ሕዝቧ አደጋ ላይ ወድቆ ለዕልቂት በተጋለጠ ጊዜ ንግሥት የነበረች ቢሆንም የህዝቧን ህይወት ለመታደግ ህይወቷን እንድትሰዋ የሚጠይቃትን ተግባር ከማድረግ ግን አልተቆጠበችም፡፡ ንግሥት በመሆኗ ያላትን አጋጣሚ ተጠቅማ ለህዝቧ እንድትቆም ስትጠየቅ ከአጎቷ የተነገራት "**ንግሥት ለመሆን የበቃሽው እንደዚህ ላለው ጊዜ እንደሆነ ማን ያውቃል?**" የሚል ነበር፡፡ እርሷም አደጋውን ብትፈራም በድፍረት በመጓዟ ሕዝቧን ለማዳን ችላለች፡፡

እናንተም እዚህ የተሰበሰባችሁ አገር ቤት ካሉት ሴቶች በተሻለ መልኩ መልካም ዕድሎች አሏችሁ፡፡ ብትናገሩ ትደመጣላችሁ፤ ብትጮሁ ትሰማላችሁ፡፡ **በትምህርት፣ በእውቀት፣ በልምድ የካበተው ችሎታችሁን ተጠቅማችሁ የመናገር መብታቸው ለተነፈገው የአገራችን ሴቶች ድምጽ መሆን ትችላላችሁ፡፡ በዚህ ጊዜ እንደዚህ ዓይነቱ ቦታ ፈጣሪ እንደትገኙ ያደረገው "እንደዚህ ላለው ጊዜ እንደሆነስ ማን ያውቃል?" ይህ የአጋጣሚ ጉዳይ አይደለም፤ በአምላክ ፈቃድ የሆነና በግል እንደ ግለሰብ፤ በቡድን ደግሞ አሁን እንደተሰባሰባችሁበት ድርጅት የተሰጣችሁን ኃላፊነት እንድትወጡ ለዓላማ ነው የተጠራችሁት፡፡**

**አገራችን ሁሉም ዓይነት ሴቶች ያስፈልጓታል፡፡ አምላክ ለዚህ የተቀደሰ ተግባር የጠራው የተማሩትንና የተሻሉትን ብቻ አይደለም፡፡ ሁሉንም እንጂ! ስለዚህም በኦሞ ሸለቆ ከንፈሮቿ ላይ ሸክላ ከምታንጠለጥለው ውብ ጀምሮ በአዲስ አበባ ከንፈሮቿን ቀይ ቀለም እስከተቀባችው ቆንጆ፤ በቤንሻንጉል ጉሙዝ ባዶ እግሯን ከተዋበችው ጀምሮ በዋንዳቢቷ እስካጌጠችው የኦሮሞ ኮረዳ፤ በኦጋዴን በሒጃብ ካሸበረቀችው ኢትዮጵያዊት ጀምሮ ባማረ ጥለት እስከተዋበችው የአማራ ቆንጆ፤ ግማሽ አካሏ እርቃን ከሆነው የአፋር ድንቅ ጀምሮ በሹርባዋ እስከተዋበችው የትግራይ ሴት . . . ሁሉም ዓይነት ሴቶች ኢትዮጵያችን ያስፈልጓታል፡፡ እነዚህ ሴቶች እናንተ ናችሁ፤ እናንተም እነዚያ ሴቶች ናችሁ፡፡ እናንተ እዚህ የተሰበሰባችሁ አገርቤት ያሉት ሴቶች ሁሉ ተወካዮች ናችሁ፡፡ አገር ቤት ያሉት ኢትዮጵያውያን ሴቶች መብት እስካልተከበረ ድረስ የእናንተ በምዕራባውያን አገራት መብታችሁ መከበሩ ብቻ በቂ አይሆንም፡፡ ለዚህም ነው የጋራ ንቅናቄያችን “ሁላችንም ነጻ ካልወጣን ማንም ነጻ ሊሆን አይችልም” የሚለውን ዋንኛ ዓላማው አድርጎ የሚንቀሳቀሰው፡፡**

ስለሆነም ዛሬ ብዙ መሰናክሎችን አልፋችሁ ለዚህ ታላቅ ስብሰባ በቅታችኋል፡፡ ዛሬ አዲስ ጅማሬ ነው፡፡ እንደናንተ ዓይነቱ በሰከነ አስተሳሰብ የሚንቀሳቀስ ቡድን መበራከት “**ከጎሣ ይልቅ ሰብዓዊነት የሚቀድምባት**” ለሴት ልጆቻችንና የልጅ ልጆቻችን የምናወርሳት አዲሲቷ ኢትዮጵያን ለመመስረት የሚያስችል መሠረት የሚጥል ይሆናል፡፡ ይህንን ጅማሬያችሁን በምንም ቢሆን ምን ልታቋርጡት አይገባም፡፡ **የጋራ ንቅናቄያችንም ከእናንተ ጋር መቆሙንና አብሮ ለመሥራትም ሆነ ለመተባበር ያለውን ዝግጁነት ስገልጽላችሁ ከፍተኛ ደስታ እየተሰማኝ ነው፡፡**

**ፈጣሪም በምታደርጉት ሁሉ መሳካትን እንዲሰጣችሁ በአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ እንዲሁም በራሴ ስም እገልጻለሁ፡፡**

አምላክ አገራችንን ይባርክ!


አክባሪ ወንድማችሁ
ኦባንግ ሜቶ
ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ ዋና ዳይሬክተር
ስልክ፡ 202 725-1616
Email: Obang@solidaritymovement.org
Website: www.solidaritymovement.org


